የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 8
ADDIS ABABA - 26th December, 2000

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፮/፲፱፻፺፫ ዓ.ም
የነዳጅ ሥራዎች ገቢ ግብር (ማሻሻያ)
አዋጅ ........................................................ገጽ ፩ሺ፬፻፴፱

CONTENTS

Proclamation No. 226/2000
Petroleum Operations Income Tax (Amendment)
Proclamation ..........................................Page 1439

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፮/፲፱፻፺፫
### የነዳጅ ሥራዎች ገቢ ግብር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የነዳጅ ሥራዎች ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፮/፲፱፻፸፮ን ማሻሻል በማስፈለጉ፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የነዳጅ ሥራዎች ገቢ ግብር (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፮/፲፱፻፺፫» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ማሻሻያ

የነዳጅ ሥራዎች ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፮/፲፱፻፸፮ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡

፩· የአዋጁ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡

"፩· በነዳጅ ስምምነት መሠረት የነዳጅ ሥራዎች የሚያካሂድ ማንኛውም ሰው ግብር ከሚከፍልበት ገቢው ላይ ፴ በመቶ (ሠላሳ ፐርሰንት) የገቢ ግብር ይከፍላል።»

፪· የአዋጁ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ ፮(ሀ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፮(ሀ) ተተክቷል፡

«(ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት ከሚሰላው የሰብ ኮንትራክተሩ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ ሰብኮንትራክተሩ ፴ በመቶ (ሠላሳ ፐርሰንት) ተመን መክፈል ያለበትን የግብር ክፍያ ይቀንሳል፡»

፫· የአዋጁ አንቀጽ ፲፭ ተሠርዟል።

፬· የአዋጁ አንቀጽ ፲፮፣ ፲፯፣ ፲፰ እና ፲፱ እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፲፭፣ ፲፮፣ ፲፯ እና ፲፰ ሆነዋል።

፫· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

### PROCLAMATION NO. 226/2000
### A PROCLAMATION TO AMEND THE PETROLEUM OPERATIONS INCOME TAX PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Petroleum Operations Inome Tax Proclamation No.296/1986;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby prolaimed as follows:

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Petroleum Operations Income Tax (Amendment) Proclamation No. 226/2000".

2. Amendment

The Petroleum Operations Income Tax Proclamation No. 296/1986 is hereby amended as follows:

1) Sub-Article (1) of Article 3 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (1):

"(1) Any person engaged in petroleum operations under a petroleum agreement shall pay thirty percent (30%) income tax on its taxable income"

2) Sub-Article 6(a) of Article 13 is deleted and replaced by the following new Sub-Article 6(a):

"a) deduct an amount of tax payable by the Sub-Contractor at the rate of thirty percent (30%) on the taxable income calculated in accordance with Sub-Articles (1) and (2) of this Article;"

3) Article 15 of the Proclamation is deleted.

4) Articles 16, 17, 18 and 19 of the Proclamation are renumbered as Articles 15, 16, 17 and 18, respectively.

3. Effective Date

This Proclamation shall enter into force as of the 26th day of December, 2000.

Done at Addis Ababa, this 26th day of December, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001